# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 39

ሕዳር 4 ቀን 1215ዓም(13-11-2022)

ባሳለፍነው ሰሞን የታዘብነውን ለመተንተን ስንነሳ የመጀመሪያ እርዕሳችን የሚሆነው መቋጫና መጨረሻ የሌለው በቀጣይነትእየተስፋፋ የሄደው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና በምዕራብ ደቡብ ያገራችን ክፍል የሚፈጽመው ያላባራው ጭፍጨፋ ነው።ብዙ ጊዜ በመደጋገም የጭፍጨፋውን መጠንና አይነት መግለጻችን አይዘነጋም።አሁንም በመቀጠሉ ከመግለጽና ወንጀለኞቹን ከማጋለጥ ወደኋላ አንልም። በአማራው ማህበረሰብ ላይ የተመዘዘው ሰይፍ ወደ አፎቱ አልገባም፤የተጠቀጠቀው የመትረዬስ ጥይቱም ከቃታውና ካፈሙዙ አልተለዬም።እንደውም ይበልጥ የዘግናኝ አገዳደሉ አይነትና መጠኑ ጨመረ እንጂ አልቀነሰም።የወራት ዕድሜ ያላቸው ህጻናት፣ምንም የማያውቁ ንጹሃን ሴቶችና አዛውንት ፣ታታሪ አርሶ አደሮች በማንነታቸው ብቻ መጨፍጨፋቸው አላባራም።አሁንም የንጹሃን እምባና ደም እንደ ጅረት ውሃ ይፈሳል።ኡኡታና የመከራ ድምጻቸው ሰሚ አላገኘም።እነዚህን ከሞፈርና ቀንበር ውጭ ያልታጠቁና ምንም በደል ያልፈጸሙ፣ለመከላከልም ያልመከቱ ዜጎችን መግደልና፣ማቃጠል የጀግና ሞያ ተደርጎ ይፎከርበታል።ለዚህ ክፉና አረሜናዊ ድርጊት አስተባባሪውና መሪው በሥልጣን ላይ ያለው የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ቡድን ስለሆነ ተከላካይ መንግሥት የለም።የድሆቹ እንባ እንደ እራሄል እምባ ለፈጣሪው አቤት ይላል።እኛም አብረን አቤት እንላለን፤ ግራ ሲገባን ፈጣሪንም ወይ ውረድ! ወይ ፍረድ! ብለን እንጠይቃለን።

ምንም እንኳን በአገራችን ሰላም ለመስፈን የሚያስችል ድርድርና ስምምነት በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል ተፈረመ ቢባልም የጭፍጨፋውና የጦርነቱ አቅጣጫ ተቀዬረ እንጂ ከነጭራሹ አልተወገደም።አገር አጥፊው የጎሳ ፖለቲካና ፖለቲከኞቹ ካልጠፉ በቀር ሰላም ይሰፍናል ማለት ዘበት ነው።በሁለቱ የጥፋት ሃይሎች መካከል የተደረሰው ስምምነት በጥቅምና በሥልጣን ድርሻ ምክንያት ተሻርሾሮ የነበረው ግንኙነታቸው እንደገና ተጠናክሮ ሃይላቸውን አስተባብረው ለዳግም ጥፋት የሚሰለፉበት ዕድል የሰጠ እንጂ፣ ከጥፋታቸው ተምረው መልካምና ትክክለኛ አቅጣጫ የሚከተሉበት እንዳልሆነ ከበቂ በላይ ገልጸናል፤ሌሎቹም እንደኛው ገልጸውታል።ከዚህ በተቃራኒው የሥርዓቱ ደጋፊና አሽቃባጮች የስምምነቱን መልክ በመለወጥ ሲያሞግሱና ሲያጨበጭቡ ይደመጣሉ።ከነዚህ መካከል የአብይ አህመድ የተንኮል አማካሪ የሆነው በተግባሩ ዳግማዊ ራስፑቲን ብለን የሰየምነው ዳንኤል ክብረት በተለያዩ ጊዜያቶች የተናገረውን ጎትተን ብናመጣ በአንድ እራስ ሁለት ምላስ የሚለው ያገራችን አባባል መሬት ላይ የማይወድቅ በመሆኑ ኩራት አድሮብናል።ይኸው ጉደኛ ቀደም ሲል ስለህወሃቶች “እነዚህ ሰይጣናዊ የሆኑ ቡድኖች ዳግም እንዳይፈጠሩ ፈጣሪን እለምናለሁ፣አስተሳሰባቸው ብቻ ሳይሆን ሥራቸው ሁሉ የሰይጣን ነው፤የክፋት ሁሉ መጀመሪያና መጨረሻ ናቸው፤ከቶም ቢሆን ወደ ደግ ነገር አያመሩም “ያለውንና አሁን ከስምምነቱ በኋላ ደግሞ 180 ዲግሪ ተቀልብሶ”በበሰለና በአስተዋይ አይምሮ ከዚህ ስምምነት ላይ መድረሳቸው በጣም አስደስቶኛል፤ለኢትዮጵያም አዲስ ምዕራፍ የተከፈተበት ስምምነት ነው”በማለት በውሸትና ክhd,ቱ ላይ የማይፋቅና የማይደበዝዝ የምላስ ማህተሙን ለትዝብት አስቀምጧል።እንዲህ ነው ወራዳነት!

የዳንኤል ክብረት ብቻም ሳይሆን ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍል የወጡ፣በተለያዩ የእምነት ተቋማት የመሪነት ቦታ የያዙ ፣ምሁራን፣ነጋዴዎች፣የመንግሥት አፈቀላጤ አድርባይ ጋዜጠኞች፣በብልጽግና ዙሪያ ተሰልፈው በድጎማ የሚተዳደሩ የፖለቲካ ድርጅት መሪዎችና አባላት ---ወዘተ የችግሩን ምንጭ እያወቁ ለመኖር ሲሉ እውነቱን ክደው ሰላም ወረደ እያሉ ሲያጨበጭቡና ሕዝቡን ሲያሳስቱ፣ እንደነሱ

የማይጭበረበረውን ወይም ለጥቅም ያልተገዛውን ተቃዋሚ የሰላም ጸር እያሉ ሲፈርጁ የታዘብንበት ሳምንት ነው።ግን እውነት ትመነምናለች እንጂ አትበጠስምና ማንኛው ትክክል እንደሆነ የምናይበት ጊዜው እሩቅ አይሆንም።በዚያን ጊዜ ማን አንገቱን ደፍቶ ማን ደረቱን ነፋቶ እንደሚራመድ ወይም በታሪክ የሚኮራውና የሚያፍረው ማን እንደሆነ ጊዜ መስታወቱ ያሳዩናል። አሁንም እንላለን ስምምነቱ የሁለት ጻረ ሰላም ቡድኖች እርቅ እንጂ የሕዝብ ለሕዝብ አይደለም።አገርን ወደ ባሰ ቀውስ የሚመራ እንጂ የጎሳ ፖለቲካን የሚያሶግድና ያገራችንን አንድነት የሚያረጋግጥ አይደለም።ሁሉም ነገር ላለፉት 32 ዓመታት እንደነበረ የሚያስቀጥል ስምምነት ነው።

የስምምነቱ ዋና ዋና ነጥቦች ምን ምን እንደነበሩ ባለፈው ዘገባችን ማቅረባችን ይታወሳል። ከነዚያ ውስጥ የትኞቹ በተግባር ሊገለጹ እንደሚችሉ የምናዬው ይሆናል። አሁን ላይ  በግልጽ ይፋ ሆኖ የወጣው የስምምነቱ አድራጊ ፈጣሪ የሆነችው አሜሪካና አጃቢዎቿ የምዕራብ አገሮች መሆናቸው ነው። ይህም እንደሚሆን ከዓመታት በፊት ጀምረን በራዲዮ ስርጭታችንም ሆነ በድረገጻችን በኢትዮ-ፓትሪዎትስ  ላይ ስንገልጸው የነበረ ጉዳይ ስለሆነ ለእኛ አዲስ ነገር አልሆነም።በጥቅሉ የአብይ ብልጽግና  ቡድንም ሆነ የወያኔዎቹ ስብስብ በመጨረሻው ላይ በአሜሪካኖች ትዕዛዝ ከመዳፋቸው ሥር ወድቀው የተባሉትን  እንደሚያደርጉ ተናግረን የነበረውን የፖለቲካ ትንቢት በገሃድ ለማዬት ችለናል። በዚህ የምንመጻደቅ ሳይሆን በእውነተኛ መነጽር የሚያይ ሁሉ ሊደርስበት የሚችል መሆኑን ለመግለጽና እኛም ብቻ ሳንሆን ሌሎቹም ለእውነት የቆሙና የፖለቲካ ብስለት ያላቸው የዩት የጋራ ግንዛቤ ነበር ለማለት ነው።

የስምምነቱን ተግባራዊነትና የሚኖረውን ፋይዳ ስንመረምር ፣ከላይ እንደገለጽነው ከሁለቱ የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች በቀር ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የሚያተርፉት ምንም ነገር የለም።ኢትዮጵያ ልታተርፍ የምትችልበት  ነገር ቢኖር ሊበትናት የተጣለባት የጎሳ ፖለቲካና በሕገመንግሥት ስም የተጫነባት  የጥፋት መመሪያ ሰነድ ሲወገድ ብቻ ነው።

የስምምነቱ ገፊ ምክንያት በአሜሪካኖች የቀረበው አስገዳጅ የዛቻ ነጥቦች  እንጂ ከሁለቱ በመነጨ ቀናነት እንዳይደለ እንረዳለን። በአሜሪካኑ ተወካይ በማይካመር በኩል ከቀረቡት አስገዳጅ ነጥቦቹ መካከል የሚከተሉት ናቸው።

ሁለቱ ቡድኖች ተደራድረው  ስምምነት ላይ ካልተደረሰ

1 ለውጭ ግንኙነትና  የገንዘብ ምንጭ የሆነው አንዱ የኢትዮጵያ አዬር መንገድ ስለሆነ፣ የኢትዮጵያ አዬር መንገድ በዓለም አቀፍ የሚያደርገውን የበረራ መስመርና አገልግሎት እንደሚከለከል

2  የዶላር ተፋሰሱን ለማገድ በአሜሪካ ከተማ በኒውዮርክ የገንዘብ ማዕከል በዋል ስትሪት(Wall Street)ዙሪያ በደላላነት የሚያገለግሉ  የኢትዮጵያ ባንኮች ተወካዮች ከውጭ ባንኮች ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንዳይኖራቸው  ማድረግ፣

3 በጦርነቱ የሞቱት፣የቆሰሉትና የተፈናቀሉት ቁጥርና የደረሰው ውድመት መጠን ይፋ እንደሚሆንና ተጠያቂነት እንደሚከተል

በነዚህ አስገዳጅ ነጥቦች ምክንያት ሁለቱም ጻረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ሳይወዱ በግድ  ወደ ድርድሩ መድረክ ላይ እንዲገቡና ከስምምነት ላይ እንዲደርሱ  ሆነዋል።ይህ የሚያሳዬው አገራት በተለይም ኢትዮጵያ ምን ያህል የአሜሪካኖችና የምዕራባውያን ጥገኛና የእጅ አዙር ቅኝ መሆናችንን ነው።ከዚህ ቅኝ አገዛዝ መውጣት የግድ ይላል።በአሜሪካኖች ደባና ሴራ የደረሰብንን በደል ማስታወስና

እንዳይደገም ማድረግ የዘለቄታው ግባችን ሊሆን ይገባል። ለዚያም ሰልፋችንን ማስተካከልና ጎራ መለዬት ተገቢ ነው።አሜሪካኖቹም ሆኑ ሌሎቹ ያውሮፓ አገራት ለኢትዮጵያም ሆነ ለቀሪ ያፍሪካ አገራት መልካም ግምትና አስተያዬት የላቸውም በዘረኝነት ከሚነዱበት ፖለቲካቸው አንጻር አፍሪካና ሕዝቧ ለነሱ የተፈጠረ አገልጋይ እንጂ እንደነሱ  በአርአያ ስላሴ የተፈጠረ የሰው ልጅ ነው ብለው አያምኑም።በቅኝ ግዛት ሲያማቅቁት፣ሲሸጡ ሲለውጡትና  የተፈጥሮ ሃብቱን ሲዘርፉት  የኖሩት ሕዝብ በትግሉ ነጻ ሆኖ መኖሩ እንደ ውስጥ እግር እሳት ሲያቃጥላቸው ይኖራል።ለዚያም የሚወስዱት የበቀል እርምጃ ሁሉ ከባድ ነው። ለአገራቸው ነጻነትና ለአፍሪካ አንድነት የታገሉት ሁሉ በነሱ ደባና ሴራ፣ ከሥልጣን ተወግደዋል፤ ህይወታቸው አልፏል።የኮንጎው ፓትሪስ ሉሙምባ፣የጋናው ክዋሜ ንኩሩማ፣ የኡጋንዳው ሚልተን አቦቴ፣የናይጀሪያው ታፌዋ ባሌዋ፣የጊኒ ቢሳው አኔስቶ ካብራል፣የቦርኪና ፋሶው ቶማስ ሳንከራ፣የሊቢያው ጋዳፊ  ---ወዘተ የበቀል ዱላ ካረፈባቸው ጥቂቶቹ ናቸው።

በአሜሪካኖችና  በአውሮፓውያኖች ፍላጎትና ትዕዛዝ የተደረሰበት ስምምነት ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ያመጣው ጥቅም የለም ስንልም ያለምክንያት አይደለም።አሁንም ቢሆን በኢትዮጵያ አዬር መንገድ የሚገባው ገንዘብ ለሕዝቡ ጥቅም የማይውል መሆኑን በመረዳት፣በባንኮቹም በኩል የሚገኘው የዶላር ተፋሰስ ለወያኔና ለኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መሪዎች የተንደላቀቀ ኑሮ የሚውል እንጂ ለአገር ልማትና እድገት ስለማይውል ቢመጣም ቢቀርም የሕዝቡን  ኑሮ ስለማይለውጠው እንደ ትልቅ ትሩፋት አድርገን አንቆጥረውም።ወደ አገር የሚገባውና ከአገር የሚወጣው ተጓዥ በሌላው አዬር መንገድ የመጠቀሙ ዕድሉ ስለሚኖር የሚቀረው ብሔራዊ ስሜቱ ብቻ ነው። የዓለም አቀፉ አቪዬሽን አስተዳደር የአሜሪካ መንግሥት ንብረት ባይሆንም ግን በአሜሪካኖች ጣልቃ ገብነት ስለሚዘወር ምናልባት ግፋ ቢል ከምዕራባውያን ጋር ያለው የበረራ ግንኙነት ይቀር ይሆናል እንጂ ከሌሎቹ አገሮች ከኤሽያ፣ከመካከለኛው ምስራቅ፣ከአፍሪካና ከደቡብ አሜሪካ አገሮች ከአብዛኞቹ ጋር ያለውና የነበረው በረራ  ሊቋረጥ አይችልም የሚል ግምት አለን።።በተጨማሪም ከሌሎች አዬር መንገዶች ጋር ባለው ጥምረት (Star Alliance)ችግሩን ሊያቃልል ይችል ይሆናል።ግን ያም ቢሆን የምዕራባውያን እጅ ስላለበት አማራጭ አይሆንም።

ይህ አዝማሚያ እነ አብይ አህመድ አዬር መንገዱን ለመሸጥ የሚያስችላቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። የአሜሪካኖቹም ፍላጎት ስለሆነ በዚህ አጣብቂኝ ውስጥ በመከተት የግዢው ባለቤት ለመሆን የጠነሰሱት ሴራ ላለመሆኑ ዋስትና የለም።ግራም ነፈሰ ቀኝ የአሜሪካኖቹ ማን አለብኝነት የኢምፔሪያሊስት ገጻቸውን አጉልቶ አሳይቷል።ኢምፔሪያሊዝም ዓለም አቀፋዊ የብዝበዛና የጭቆና አቅምና ባህሪ ስለሆነ ትግሉም ዓለም አቀፋዊ መልክ ይኖረዋል።ለዚያም ነው ጸረ አሜሪካ ትግል በያቅጣጫው የተቀጣጠለው።ትግሉ ግልጽ ጦርነት ባይሆንም በፖለቲካውና በኤኮኖሚው ዘርፍ ተካሮ ይገኛል። ኢትዮጵያም አገር ወዳድ መሪዎች ሲኖሯት በዚያ የልዑላዊነት ትግል ጎራ ውስጥ መግባቷ የማይቀር ይሆናል።አሁንም ቢሆን ለአሜሪካ እጅ በሰጡት የጎሰኞች ጎራና ባልሰጡት አገር ወዳዶች መካከል የሚካሄደው ትግል የዚያው የጸረ ኢምፔሪያሊስት ትግል አካል ነው።

ዕድሜ ለብራዚል፣ሩስያ፣ሕንድ፣ቻይናና ለደቡብ አፍሪካ የብሪክስ (BRICS) ስምምነት ዓለም ሌላ አዲስ አሠራርና የግንኙነት መረብ ዘርግታለች።በዶላር፣በኢሮና በፓውንድ የመነገዱና ጥገኛ የመሆኑ ነገር እያበቃለት ነው።

ለኢትዮጵያም ሆነ ለቀሩት ያፍሪካ አገሮች የሚያዋጣቸው የምዕራቡ ወይም የምሥራቁ ጎራ ሳይሆን የራሳቸውን ጎራ ማጠናከር ነው።የራሳቸው የመገበያያ ፍራንክ ወይም ከረንሲ (አፍሮ) ቢኖራቸው ከውጭ ከረንሲ ጥገኝነት ለመላቀቅ ይችላሉ።ለዚህ ግን እውነተኛ የአፍሪካ መሪዎች መኖር ይጠይቃል። ባሉት  መሪዎች የሚሳካ አይደለም።አብዛኛዎቹ የምዕራባውያን በተለይም የአሜሪካኖች ቡችሎች

ናቸው።በነሱ ፈቃድ ሥልጣን የያዙ በመሆናቸው ከነሱ ቃል አይወጡም።ከአገራቸው ሕዝብ እዬሰረቁ የሚያከማቹትም በምዕራባውያን ባንክ ስለሆነ ያንን እናጣለን በማለት የተባሉትን ከማድረግና አገራቸውንና ሕዝባቸውን ከማስጠቃት አይመለሱም።የኛዎቹን ከመንግሥቱ ሃ/ማርያም ጀምረን ብንመለከት ብዙ ወንጀል ፈጽመው፣ገለውና ዘርፈው ሳይጠዬቁ በነጻነት ለመኖር የቻሉት በዚሁ የባርነት ግንኙነታቸውና አገልግሎታቸው ነው።ወያኔና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናም የዚህ ትሩፋት ተቋዳሾች ናቸው።

ለመሆኑ የሁለቱ ኢሕአዴጋውያን ስምምነት ምን ችግር ገጥሞታል ?ብለን ስንጠይቅ

በወያኔ በኩል በሦስት ጎራ ተከፍሎ እርስ በርሱ መባላቱን ለማዬት ችለናል።አንደኛው የሕዝቡ አብዛኛው ስምምነቱን ሙሉ ለሙሉ የተቀበለ፣ሁለተኛው በከፊል የተቀበለና ሦስተኛው በጭራሽ ያልተቀበለ ነው።በተለይም የትጥቅ መፍታቱ ጥያቄ በዋናነት የክፍፍሉ ምክንያት ሆኗል።ይህ ጉዳይ በኬንያ ዋና ከተማ ናይሮቢ ውስጥ በሚካሄደው የሁለቱ ቡድኖች የጦር መሪዎች የትጥቅ ማስፈታቱ ድርድር ላይም የተከሰተ የልዩነት ነጥብ ሆኗል።በተራው ሕዝብ በኩል በሰላም መኖር ቀዳሚነት የተሰጠው ሲሆን በታጠቀው በአንዱ ክንፍ በኩል ለወደፊቱ ኑሮው የሚበጀው ታስቦለት፣የሥራ ዕድል እንዲሰጠው፣ ላለፈውም ጉዳቱ ታይቶ ካሳ የሚጠይቅ ነው።በሦስተኛው በኩል የሚታዬው ተቃውሞ መሣሪያ አላወርድም ብሎ ሜካ የቀረው ታጣቂ ክንፍ ከውጩ ካለው የትግራይ ተወላጅ ጋር በመሆን የታገልነውና ብዙ መስዋእት የከፈልነው ትግራይ ነጻ አገር ትሆናለች ብለን እንጂ በእርቅና በድርድር ወደ ነበርንበት ለመመለስ አይደለም የሚል ነው።እዚህ ላይ የዬትኛው ወገን አቋም ሚዛን እንደሚደፋ የምናዬው ይሆናል።በእርግጠኛነት ግን የሰላም ድርድሩ ብዙ ውጣ ውረዶችን ማለፍ እንዳለበት ሲሆን ላለመሳካቱም ብዙ ምልከቶች እዬታዩ ነው።ሁለቱም ቡድኖች የሚታመኑ አይደሉም።በውስጣቸው ጥርጣሬና ተንኮል አይጠፉም።በደፈናው እባብ ለእባብ ይተያያል ካብ ለካብ እንደሚሉት ነው። ወያኔዎቹ በጉድጓድ ውስጥ የሚያስቀምጡት መሣሪያ ሊኖር እንደሚችል ካለፈው ስራቸው መረዳት አያቅትም።በጦርነት የሚኖር ቡድን መሳሪያ ይፈታል ብሎ መጠበቅ ጅልነት ነው።

በአሜሪካኖቹ በኩል ይበልጥ ትኩረት የተሰጠው የኤርትራ ወታደር የመውጣቱ ጉዳይ ሲሆን በወያኔ መሪዎቹም በኩል ትጥቅ ለመፍታት እነደ ዋና ቅድመ ሁኔታ ተቀምጧል።ይህ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ሁሉም በጉጉት የሚጠብቀው ነው።ኢሳያስ አፈወርቂ ወታደሮቹን ለማስወጣት ይፈልግ አይፈልግ፣ለደህንነቱ ዋስትና ይጠይቅ አይጠይቅ፣ አይታወቅም።አብይ አህመድም በዚህ ላይ ያለው አቋምም ግልጽ አይደለም።እርግጠኛ ሆኖ መናገር የሚቻለው አብይ አህመድ ሥልጣኑ እስካልተነካበት ድረስ ኢሳያስን መክዳቱ እንደማይቀርና አሜሪካኖችም ውጋ ካሉት ከጦርነት እንደማይመለስ ነው።

ከወያኔ በኩል ብቻም ሳይሆን በአማራው ማህበረሰብና በኦሮሞው በኩልም ትልቅ ጥርጣሬና ተቃውሞ በመነሳት ላይ ነው።

በኦሮሞዎቹ የኦነግ ቤተሰቦች ከሆኑት በአንዱ በነጃዋር ካምፕ በኩል የተነሳው ጥያቄ ጨፍጫፊው ኦነግ ሸኔ ለድርድር ይቅረብ የሚል ሲሆን የሚፈጽመውን የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ወንጀል አድርጎ አልተቀበለውም።ቡድኑን ለሙብት የሚታገል ሃይል አድርጎ ስሎታል።ይህ የሚያሳዬው ሁሉም የኦሮሞ ድርጅቶች የአብይ አህመድ ብልጽግናን ጨምሮ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ላይ የሚፈጸመው ወንጀል ጉዳያቸው እንዳልሆነ ነው። ጥያቄያቸው የሚያሳዬው የአማራ ነፍስ የሰው ልጅ ነፍስ እንደሆነ የማይቆጥሩት ከመሆኑ በላይ ለጨፍጫፊው በግልጽና በስውር ተባባሪ መሆናቸውን ሲሆን በተረፈ ለዘላቂ ሰላምና ለአገር አንድነት እንዳልቆሙ የሚያረጋግጥ አቋም ነው።

በአማራው በኩል የተነሳው ተቃውሞ የቆዬ ቢሆንም አሁን ሊያገረሽበትና ሊጦዝ የቻለበት ምክንያት የወልቃይትና ጠገሌ፣የራያና አዘቦ ጉዳይ በስምምነቱ ሰነድ ላይ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ይፈታል የሚለው አባባል በመስፈሩ ለአማራው የሚዋጥለት አልሆነም።እነዚህን ለም ቦታዎች የአብይ አህመድ የብልጽግና ስብስብ በሸወዳ ከአማራው ማንነት ነጥቆ ለትግራይ ማንነት፣ ለወያኔ አሳልፎ ለመስጠት በባሕርዳር ከተማ በምስለኔው በባአዴን በኩል በተጠራ ስብሰባ ለማስፈጸም የሚከተሉትን ሦስት አማራጮች ይዞ ቀርቧል።አማራጮች ተባለ እንጂ በተለያዬ መንገድ ከአማራው ነጥቆ ለማስረከብ የቀረቡ አሳሳች አካሄዶች ናቸው።

1 በፌዴራል ስር መተዳደር፣

2 በሪፌራንደም ይወሰን፣

3 ራስ ገዝ ይሁን

ሶስቱም ከአማራው እጅ ለማሶጣት የተቀመሩ ሴራዎች ናቸው።ራስ ገዝ ከሆኑ በቦታዎቹ ላይ የይገባኛል ጥያቄ በወያኔዎቹ በኩል ቢነሳና ወረራ ቢፈጸም የአማራው ክልል የእኔ ነው ብሎ ሊዋጋ አይችልም፤ የወልቃይትና የራያ ሕዝብ ብቻውን ይፋለማል ማለት ነው።

በፌዴራሉም ስር ይሁኑ ቢባል የፌዴራሉ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ሕዝበ ውሳኔ ይደረግበት ከሚለው ድንጋጌ አያመልጥም፣

የዚሁ ተመሳሳይ የሆነውም በሕዝበ ውሳኔ ይፈታ ቢባል በስምምነቱ ቀድሞ የነበረው ነዋሪ ይመለስ ስለተባለ በወያኔ የሰፈረው ሕዝብ በቦታው ተመልሶ ድምጽ እንዲሰጥበት ተደርጎ ቦታዎቹ የወያኔ ይዞታነታቸው ይረጋገጣል ማለት ነው።የአውሮፓውያኑም ሆነ የአሜሪካኖቹ ውሳኔና ፍላጎት ቦታዎቹ በዚህም ሆነ በዚያ የትግራይ ሆነው እንዲቀሩ ነው።

እነዚህ ሦስት የጥፋት መንገዶች እንዲቀበሉ የተጠሩት የወልቃይትና የራያ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴ አባላት አሻፈረን በማለት የስብሰባ አዳራሹን ጥለው እንደወጡ የተሰማ ሲሆን፤ በራያና አዘቦ ስም በስከጀርባ የኦነግ እንደራሴ በሆኑት የወሎ ህብረት አባሎች በፌዴራሉ ሥር መሆኑን ተቀብለው መፈረማቸው ይፋ ሆኗል።የራያና አዘቦ የሕዝብ ተወካዮችና ሕዝቡ ይህንን ሴራ በመቃወም አሻፈረኝ ያለ ሲሆን ተከታዩ ምን እንደሚሆንና ምንስ እንደሚከሰት ሁሉም የሚጠባበቀው ጉዳይ ነው። ለማንኛውም እራስን ማዘጋጀት ይገባል።የኦነግ ኦሕዴድ የብልጽግና ቡድንና የወያኔ ቡድን እስካሉ ድረስ ዘላቂ ሰላምና የአገር አንድነት አይረጋገጥም፤የአማራውም መብት አይከበርም።

ሁሉንም ክስተቶች ስናጤን አገራችን ከባሰ ቀውስና ጦርነት ውስጥ ትገባለች የሚለው ስጋታችን ከፍተኛ ነው።በተለይም በጦርነቱና በዬቦታው ለፈሰሰው የንጹሃን ደም፣ለጠፋው ሕይወትና ለወደመው ንብረት፣ ፍትሕ ሳይሰጥ ተሸፋፍኖ እንዲቀር የተያዘው መንገድ ለዘለቄታው ሰላም መደፍረስ ምክንያት ይሆናል እንጂ ሰላም አያመጣም።ለሰብአዊ መብት ፊታውራሪ ነኝ የምትለው አሜሪካና ተከታይዋ አውሮፓውያን ይህንን ትልቅ ፍትሃዊ ሚዛን እንዲዛባ ማድ,ጋቸው፤የሚጠቅማቸውና ለነሱ ያደረው በሰራው ወንጀል እንዳይጠዬቅ ፣ለነሱ ያላደረና ለመብቱ የቆመው የሚቀጣበት የበቀል ዱላ ማድረጋቸው ምን ያህል ጸረ ፍትሕ ለመሆናቸው ተጨማሪ ማረጋገጫ ነው።

በተከታይ ቀናት ውስጥ የወያኔ ቡድን በፓርላማው የተለጠፈበት ያሸባሪነት ስያሜ እንደሚነሳለት በስምምነቱ ሰነድ ላይ የሰፈረ ሲሆን ውሳኔ እንደሚሰጠው የሚወጡት መረጃዎችና የሚኬድበት አቅጣጫ ያረጋግጣሉ።ይህንን ተከትሎ በሰላም ስም ብዙ ወንጀል የፈጸመው የኦነግ ጨፍጫፊ ቡድንም

ለድርድር ቀርቦ ለተመሳሳይ ዕድል እንደሚበቃ የሚሸተው የፖለቲካ ጭስ ያመላክታል።ይህ በእንዲህ እያለ በሽዎች የሚቆጠሩ የአማራ ፋኖና የአማራ ልዩ ሃይል አባላት በእስርቤት እዬማቀቁ ይገኛሉ። እነሱን እያሰቃዬ ከሚኖር የብአዴን ከሃዲ ቡድን በኩል ለአማራው ማህበረሰብ የሚበጅ ቁም ነገር ይገኛል ብሎ መጠበቅ ሞኝነት ነው።የአማራው ተወላጅ ያለው ብቸኛ አማራጭ እራሱን አደራጅቶና አንድ ሆኖ ለመብቱና ለአገሩ አንድነት በሚፈይደው ትግል መሰማራት ነው።በውጭ ሃይል መተማመኑን ማቆም አለበት።ጠላትና ወዳጅን ማወቅ የትግል መጀመሪያ ነው። ከሌላው ማህበረሰብ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚቆሙትን ወገኖቹን መቅረብና ማደራጀት ተግባሬ ሊለው ይገባል።ከአማራው በላይ ለአማራው የሚታገለውንና መከራ የሚቀበለውን አንጋፋውን ኢትዮጵያዊ የወላይታ ምሁር ታዲዎስ ታንቱንና መሰሎቹን ሊታደጋቸው ይገባል። አቶ ታዲዎስ ታንቱ ፣ተመስገን ደሳለኝ፣ጎበዜ ሲሳይና ሌሎችም እንዲሁም በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ የፋኖና የልዩሃይል አባላት በግፍ ታስረው በሚሰቃዩበት አገር ሰላምና ፍትሕ ይሰፍናል ተብሎ አይጠበቅም። ከአንድ ቀን በፊት ጋዜጠኛ ጎበዜ ሲሳይ በመቶ ሽከ ብር ዋስትና የተለቀቀ ሲሆን ተመስገን ደሳለኝ ግን በተለዋች ቀጠሮ ወደ ነበረበት እስርቤት ቤት ተመልሷል።ንጹሃnne እያሰሩ የገንዘብ ዋስትና መጠዬቅ አዲስ የገቢ ምንጭ ተደርጎ ስለተወሰደ በሌሎቹ ላይ ብዙ የገንዘብ ዋስትና እንደሚጠዬቅ መገመት አያዳግትም። ተቃዋሚውን አካል፣በመንፈስና በገንዘብ ማድቀቅ የሥርዓቱ አይነተኛ መገለጫዎች ናቸው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ክስተቶች ባዬንበትና በሰማንበት ሰሞን አገር ጉድ ያሰኘ የአድርባይነት ድርጊትም ለመታዘብ ችለናል። በውጭ አገር ኑሮው በተሰማራበት የጽዳት ሥራ ያካበተውን ልምድና ተመክሮ አገሩ ይዞ በመግባት የአዲስ አበባን ቆሻሻ በመጥረግ በሕዝቡ ጋሼ አበራ ሞላ በመባል የሚታወቀው ክራር መቺ ስለሽ ደምሴ በአንድ የስብሰባ አዳራሽ መድረክ ላይ የአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ዓይንሽ ላፈር ያላትን የአነግ የመንፈስ ልጅ የሆነችውን አዳነች አቤቤን ባልተወለደcb,ት ጊዜ ከተከናወነው ከአፍሪካ አንድነት ምስረታ ጋር አቆራኝቶ ለማመስገን የሄደበት መንገድ እንኳንስ የሚያውቁትን የማያውቁትንም ያሳዘነና ያሳፈረ ነበር።ይህንን ቅሌት ያዩ ብዙዎቹም ምነው ባይበላ ቢቀር ብለውታል።እኛም እንዲህ ውልግድግድ ያለ ግጥምና ድምጽ ይዞ፣ያንገቱ ደምሥር እስኪወጠር ድረስ በመድረክ ላይ ወጥቶ ኪነትን የከተማ ቦታ ወይም የኮንዶ መለመኛ አድርጎ ሲያዋርደው ምነው ባለሙያዎቹ ዝም አሉት ብለን እንጠይቃለን።ሌሎቹንም የኪነት ሰዎች ከዚህ አይነቱ ኪሳራ ይጠብቃችሁ!ሌላው ቢቀር ለህሊናችሁ እደሩ ለማለት እንወዳለን።

የጎሰኞች ስምምነት ዘላቂ ሰላም አያወርድም!

ሁሉም አገር ወዳድ ለአገር አንድነትና ለእውነተኛ ሰላም ይታገል!!